የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# የ2014 በጀት ዓመት የ8 ወራት አፈጻጸም ሪፖርት

መጋቢት-2014

አዲስ አበ

## 1. መግቢያ

ሚኒስቴር መ/ቤታችን የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት ከቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተለይቶ እራሱን ችሎ እንዲቋቋም ሲደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቶች የተሰጡ የወል ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን እንዲሁም ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን፣ የአገሪቱ የወጪ ንግድ ሰለሚስፋፋበትና ስለሚጠናከርበት፣ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ስለመቆጣጠር፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ስለመዘርጋትና የማዘመን፤የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ የማጥናት፣ የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን የማስተባበር፤ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን የመቆጣጠር እና ከንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣ እና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጡትን ተግባራት በመስራት በንግድ አሰራሩ ላይ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን በማስተካከል ተገልጋዮችን ለማርካት በትኩረት እየሰራ ይገኛል።

በዘህም መሰረት ባለፉት 8 ወራት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትኩረት መስኮችና የተኩረት መስኮቹን ለማሳካት ከተቀረጹ ግቦች አኳያ የተካናወኑ ዋናዋና ተግባራት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ መፍትሄዎችን በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2. የትኩረት መስኮች

### 2.1 የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ግንባታ

#### 2.1.1 የአረጃጀትና ተቋማዊ የለውጥ ስራዎች

የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቃቀር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ በፊት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ ተቋቁሞ የነበረውን ሚኒስቴር መ/ቤት በሁለት በመክፈል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ ተለይቶ እንዲቋቋሙ የፌዴራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት መቋቋሙ የሚታወቅ ነው፡ ፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 (እንደተሻሻለ) እና በአዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለ) ተቋቁመው የነበሩትን የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ከዳኝነት ችሎት ውጭ ያሉ ሥራዎች ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአዋጅ ተሰጥቷል፡፡

በአዲሱ የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱን ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ቀድሞ  ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የነበሩ እና ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ የተቀላቀሉ ባለስልጣን መ/ቤቶች ባለሞያዎችን ያካተተ የአደረጃጀት የጥናት ቡድን በማቋቋም በ3 ዘርፍ ፣ በ7 መሪ ሥራ አስፈጻሚ እንዲሁም በሚኒስትር ጽ/ቤት እና የስራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያካተተ የማሻሻያ  አደረጃጀት ተሰርቶ በበላይ አመራሩ ከጸደቀ በኋላ Higher Level Map፣ የሚያስፈልገው የሰው ሀይል እና የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተልኮ የምዘናና ደረጃ መስጠት ሥራ በኮሚሽኑ በኩል የጸደቀ ሲሆን በመመሪያው መሰረት  የሰራተኛ ድልድል ለማድረግ የድልድል ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ለመግባት የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱን አዲስ አደረጃጀት ተከትሎ ተግባርና ኃላፊነታቸው  ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀላቀሉ  የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣንን ባካተተ መልኩ የመዋቅር ማሻሻያየተዘጋጀ ሲሆንበሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጸድቆ የሰራተኛ ድልድል ለማድረግ የድልድል ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡መንግሥት የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሲጠቀምብት የነበረውን መ/ቤት ለሚኒስቴር መ/ቤታችን የተሰጠ

በመሆኑ የህንጻ እድሳትና ጥገና ዲዛይን ተዘጋጅቶ ለሰራተኛውና ለተገልጋዮች ምቹና ሳቢ የሥራ አካባቢ ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡

### 2.1.2 የፈጻሚውን አቅም ከማሳደግ አንጻር

ከISO /International Standardization Organization/ 17020 ጋር በተያያዘ ኢንስፔክሽን ላይ፣ በሶላር ምርቶች ጥራት ቁጥጥር፣በተሸሻለው የንግድ ሕግ፣የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 ደንብና መመሪያ፣ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን አሠራር ማኑዋል፣በአፍሪካ ነጻ ንግደ ቀጣና ድርድሮች (በአገልግሎት ንግድ፣ በንግድ ውድድር ፖሊሲ እና በኤሌክትሮኒስ ንግድ (E-Commerce)) ላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት እና አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለባለድርሻ አካላት፣ለክልሎችና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች በድምሩ ወንድ 263 ሴት 12 በድምሩ ለ 275 ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

### 2.1.2 የህግ ማዕቀፎች ዝግጅት

ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ በረቂቅ ደረጃ የተጠናቀቀ ሲሆን ሰነዱን በውይይት ለማዳበር ወንድ 69 ሴት 11 በድምሩ 80 ለሚሆኑ ከልዩ ልዩ የመንግስት ተማት፣የግል ተማት፣መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለማቀፍና ሀገር ከአቀፍ ድርጅቶች የተዉጣጡ አመራሮችና ባለሞያዎች በተገኙበት ዉይይትና ተጨማሪ ግብዓት የማሰባሰብ ስራ ተሰርቶ የተገኙት ግብዓቶች የማካተት ሥራ ተከናውኗል፡፡ በጠቅላላው ወንድ 343 ሴት 24 በድምሩ ለ367 ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲ ዝግጅት በተመለከተ፡-** የሀገሪቷ ማንኛውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ላይ መንግስት ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየትና ከዚያም ጋር ግንኙነቱ መጠናከሩ ከፍተኛ የሆነ ትብብርና ቅንጅት እንዲታይበት ማድረግ መቻሉን ለማሳየት ጠንካራ የጥራት መሰረተ ልማት ውጤታማና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማስቻል የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ግብዓት ተሰባስቦ ለመጨረሻ የValidation Workshop ተዘጋጅቶ ውይይት የተደረገበት ሲሆን የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጸደቀ በኂላ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚላክ ይሆናል፡፡

**የሀገር ውስጥ ነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ** የዓለም አቀፉን ዋጋ በሚያንጸባርቅ መልኩ እየታየና በየጊዜው እየተከለሰ ወደ ሸማቹ እንዲተላለፍ ባለመደረጉ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ እዳ በዋጋ

ማረጋጊያ ፈንዱ ላይ እየተከማቸ ይገኛል። በመሆኑም ጎልተው የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የነዳጅ ግብይት ሪፎርም በሀገር ደረጃ በእቅድ ተይዞ እየተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እየሰፋ የመጣውን በፖሊሲ ያልተደገፈ የነዳጅ ድጎማ ከተመረጡ ተሽከርካሪዎች በሂደት ለመቀነስና ለማስቀረት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ሲደረግበት ቆይቶ የተሰጡ ግብዓቶችን በማካተት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቦ ምክር ቤቱ ታህሳስ 20 ቀን 2014 ዓም ባደረገው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ጸድቆ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በተቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ አማካኝነት ክልሎችን ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈጸም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እየተሰራ ይገኛል።

ላለፉት 25 ዓመታት በስራ ላይ የነበረውን **የነዳጅ ውጤቶች የዋጋ ግንባታና ትርፍ ህዳግ** አሰራር በማሻሻል ወጥነትና ግልጽነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኂላ የተሰጡ ግብዓቶችን በማካተት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቦ ምክር ቤቱ ታህሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ባደረገው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ጸድቆ በውሳኔው መሠረት ወደ ሥራ ለመግባት ኩባንያዎች ማዘጋጀት የሚገባቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንዲሰሩ የኢትዮጵያ የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ጉዳዩን በዋናነት በመያዝ በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል። በተመሳሳይም **ከቀረጥ ነጻ የገቡ ምርቶች የአሰራር ማኑዋል** ተዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋጋ ማረጋጋት ግብረ-ኃይል ቀርቦ የተሰጠውን ግብዓት በማካተት ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ሃገሪቱ ከውጭ ሃገር በመንግስት ድጎማ የምታስመጣው የምግብ ዘይት በሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች በማምረት ቀስ በቀስ የምግብ ዘይት ፍላጎት በሀገር ውስጥ ለማሟላት እና ከአቅርቦት እስከ ስርጭት ያለውን የንግድ ሰንሰለት ቁጥጥርና ድጋፍ ለማድረግ የፓልም የምግብ ዘይትን የሚያጣሩ የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የምርት አቅርቦት፣ ስርጭት እና የዋጋ ግንባታ አሠራር ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኂላ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

የቁም እንስሳት ወጪ ንግድ የመሸጫ የገበያ ማነፃፀሪ ዋጋ መመሪያ እና የቁም ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ሀገራዊ ጥቀቅምን ለማስከበር እንዲቻልና በመስኩ የሚታየውን ከዋጋ በታች አሳንሶ በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ግኝታችን ማሳጣትና በመስኩ የኮንትሮባንድን ንግድ እየተስፋፈ መምጣቱን ለመግታት የሚያስችል **የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ**

***መመሪያ*** በማዘጋጀት በመመሪያው መሰረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የቁም እንስሳት ንግድን ፖሊሲ አስፈላጊውን ግብዓት ከኢትዮጵያ የፖሊስ ጥናት ኢንስቲትዩት የተሰጠውን ግብዓት በማካተት እንዲሁም ከብሔራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰጠውን አስተያየትና አቅጣጫ በማካተት የመጨረሻ ሰነድ ዝግጅት በማጠናቀቅ ለብሔራዊ ኮሚቴ ለመላክ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የኤክስፖርት ልማት ስትራቴጂ ዝግጅትን በተመለከተ በወጪ ንግድ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በተለይም ለወጪ ንግድ ምቹ የሆነ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር፣የምርቶችንና አገልግሎቶችን ስብጥር በማስፋት እና አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ቁጥር በመጨመር ከወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የኤክስፖርት ልማት ስትራቴጂ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ውይይት እየተደረገበት ይገኛል፡፡

የግብይት ስርዓቱን አጭር እና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፣ ለወጪ ገበያ እና ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በመጠን እና በጥራት ለማሻሻል እና የፋይናንስ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር **የእቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት ደንብ** ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በተጨማሪም **የእቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት *መመሪያ*** ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡የእቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት በማስያዣነት በመጠቀም የፋይናንስ አገልግሎት ለማግኘት ከብሄራዊ ባንክ እና ከህብረት ስራ ማህበራት ጋር በመተባበር በማህበራትና በአቀናባባሪዎች በተመረጡ ምርቶች ላይ የሙከራ ትግበራ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡

የጫት ግብይት መመሪያ ከ41 ዓመት በፊት ተዘጋጅቶ የቆየ በመሆኑ የሀገራችን ጫት አምራቾች ከወጪ ግብይቱ ተጠቃሚ ሳያደርጋቸው በመቆየቱ እና ሀገራችንንም ከጫት ንግድ ማግኘት የሚገባትን ገቢ በማሳጣቱ ከተለያዩ መ/ቤቶች በተውጣጡ የጥናት ቡድኖች በተደረገ ጥናት ችግሩ በግልጽ የሚታይ መሆኑ ስለታመነበት **የጫት ምርት ግብይት *መመሪያ*** እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የጫት ምርት የውጪ ንግድ አሰራር እና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በማክሮ ኮሚቴ ለማጸደቅ በዝግጅት ላይ ይገኛል

የወጪ የግብርና ምርቶችን በመጠን እና በጥራት በማሻሻል እንዲሁም ለወጪ ምርት አቅርቦት አመራጭ የግብይት ስርዓት እንዲኖር እና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን **የውል እና የኢንቨስትመንት እርሻ ልማት የምርት ግብይት የአሰራር ስርዓት *መመሪያ*** በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

**የጤናና ደህንነት የመለኪያ መሳሪያ እና የታሸጉ ምርቶች** የተጣራ መጠን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጀ ሲሆን የህጋዊ ስነ-ልክ አዋጅ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ግብአቶች የተሰበሰበ ሲሆን **የአውቶ ቦቴ ቬሪፊኬሽን ማዕከል ዘመናዊ** ለማድረግ የሚያስችል የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

ከዚህም በተጨማሪ በአውቶ ቦቴ እና በተሽጋጋሪ ሚዛን የሚሰጠው የቬሪፊኬሽን አገልግት አሰጣጥ ወደ ኢሰርቪስ በማስገባት **በኦን ላይን አገልሎቱ** እንዲሰጥ ለማድረግ የማልማት ስራው በማተናቀቅ የፓይለት ሙከራ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች በመሰራት ይገኛሉ።

**የህጋዊ ስነ-ልክ ባለሙያዎችን** አቅም ለማሳደግ በተግባረዕድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት ዘላቂነት ለማስቀጠል ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስትቲዩት እና የተግባዕረድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የሶስትዮሽ **የመግባቢያ ስምምነት** ፊርማ ተካሂዷል።

የአስራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ አሠራር፣ የፋብሪካ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሠራር እና የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር **አሠራር ረቂቅ ማኑዋሎች** ተዘጋጅተው ለውይይት ቀርቧል። የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር የአሰራር ማንዋል የማሻሻል ስራ በመከናወን ላይ ይገኛል። የንግድ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር የአሰራር ረቂቅ መመሪያ የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ይገኛል።

የቅድመ-መላኪያ ፍተሻ ዓላማዎች የሸቀጦቹን ብዛትና ጥራት የማረጋገጥ እና ምርቶች የመድረሻ ገበያውን የደህንነት መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ በህብረተሰቡ ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ነው ። በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤታችን የተስማሚነት ምዘና መርሃ ግብር ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም መሰረት ከውጪ የሚመጡትን ምርቶች ጥራት በመቆጣጠር ጥራታቸውን ለማረጋገጥ ከኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመተባበር በሶላር ቴክኖሎጂ **የተስማሚነት ቅድመ-ማረጋገጫ** /Pre-shipment verification of conformity/ አሰራር ተግባራዊ ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል።፡

**የአስገዳጅ ደረጀዎች ማስፈጸሚያ አዋጅ** በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለማጸደቅ በሂደት ላይ ይገኛል።

በአምስት የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ቅ/ጽ/ቤቶች የተጀመረውን የጉሙሩክ የአንድ መስኮት አገልግሎት በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት ለማስገባት እየተሰራ ይገኛል።

## 2.2 ቀልጣፋ፣ዘመናዊና ተደራሽ የንግድ አሠራር

### 2.2.1 የንግድ አሰራር ስርዓቱን ማዘመንና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን በቴክኖሎጂ ተደራሽ ማድረግ

የዓለም ባንክ የዓለም ሀገራትን የንግድ ሥራ አመችነት (Doing Busines) አስመልክቶ እ.ኤ.አ በ2018/19 ባወጣው ሪፖርት መሰረት ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ190 ሀገራት የንግድ ሥራን ለመጀምር ያለ አመቺነት (Ease of starting a Business) 168ኛ እንዲሁም በንግድ ሥራ አመቺነት (Ease of doing Business) 159ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኗን ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

የንግድ አሰራር ስርዓቱን በማዘመን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ በ2022 የንግድ ስራ ለመጀመር ያለ አመቺነትን አሁን ካለበት 48 ነጥብ ወደ 80 ነጥብ ከፍ በማድረግ በ2022 ከምርጥ 50 አገሮች ተርታ ለማሰለፍ እየተሰራ ይገኛል፡፡ መንግስት ወደ ንግድ ሥራ ለሚገቡ የንግዱ ማሕበረሰብ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ የጊዜና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎትን ለተገልጋዩ ለማቅረብ፣ የተገልጋዩን ውጣ ውረድና እንግልት ለማስቀረት፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገራችንን ገፅታ በመገንባት ንግድና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልገሎትን በኦላይን ተደራሽ ለማድረግ የሪፎርም ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዚህም መሰረት በሀገራችን የንግድ ሥራን ለመጀመር በአማካይ 32 ቀናት እና 11 ሂደቶችን (Procedures) ማለፍ የሚጠይቅ የነበረ ሲሆን በተሠራው የሪፎርም ሥራ ቀናቶችንና ሂደቶችን በማሻሻል በአማካይ ወደ 5 ቀናት እና 4 ሂደቶች (Procedures) ዝቅ እንዲሉ ተደርጓል፡፡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008፣ ደንብና መመሪያ የማሻሻል ሥራም ተሰርቷል፡፡ ቀደም ሲል 1,500 የነበረውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መስጫ መደብ ወደ 519 ዝቅ እንዲል እንዲሁም ብቃት ሲጠየቅባቸው የነበሩ 1,350 መደቦች ወደ 52 ዝቅ እንዲሉ የተደረገ ቢሆንም ባለፉት 8 ወራት በጥናት ላይ በመመስረት በተሰራው ሥራ ወደ 10 ዝቅ እንዲሉ በማድረግ በተገልጋዩ ላይ ሲደርስ የነበረውን እንግልት ለመቀነስ ተችሏል፡፡

ይህም ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ከሩዋንዳ 5 ሂደቶች እና 4 ቀናት እንዲሁም ከኬንያ 11 ቀናት ይወስድ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ሀገራችን የንግድ ሥራን ለመጀመር ባለ አመቺነት ከፍተኛ ለውጥ

እንዳመጣችና የደረጃ ተወዳዳሪነትና ገጽታ በመለወጥ የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡

በቀጣይ አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ የኤሌክትሮነክስ እና የህትመት ሚዲያዎችን በመጠቀም ለንግዱ ማህበረሰብ አገልግሎቱን የማስተዋወቅና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ የመስራት፣ የክልሎችና ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎችን አቅም የማሳደግ፣ የንግዱ ማህበረሰብ ለሚገጥመው የአጠቃቀም ችግር የኢንተርኔት ካፌዎችን በማሰልጠን አገልግሎቱን ተደራሽ የማድረግና የሥራ ዕድል ጭምር የመፍጠር እንዲሁም የኦንላይን ክፍያ ጋር ተያይዞ የሚስተዋለውን ችግርን ለመቅረፍ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ  የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመፈጸም  ስምምነት የተደረገ ሲሆን በሌሎች የግል ባንኮችም አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ከኢትየጵያ የኤልክትሮኒክስ ክፍያ አስፈጻሚ ድርጅት ጋር በጋራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የንግድ ዘርፉን በቴክኖሎጂ በማዘመን የሚሰጠውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አገልገሎት ለማሳለጥ በጠቅላላው በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት 1,134 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መካከል 1,082 (95.4%) ጣቢያዎች አገልግሎቱን ከአንድ መረጃ ቋት እንዲያገኙ የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ሶፍትዌር በማልማት ከኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሥርዓቱ ጋር ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ እለታዊ የነጋዴዎች መረጃ የመለዋወጥ ስርዓት ተዘርግቶ አገልግሎቱ እየሰጠ ይገኛል፡

ባለፉት 8 ወራት በአገር አቀፍ ደረጃ 2,508,670 ንግድ ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 1,910,622 (88.6%) አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 24,794 በኦንላይን አገልገሎት ለመስጠት ታቅዶ 15,626 (63%) ተከናውኗል፡፡

በአፋርና አማራ ክልል የትግራይ ወራሪ ቡድን በፈጸመው ውድመት የንግድ ፈቃዳቸውን ማሳደስ ያልቻሉቱን የንግዱ ማህበረሰብ ችግራቸውን በማየት የንግድ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ ሚኒስቴር መ/ቤታችን  በሰጠው አቅጣጫ መሰረት በአማራ ክልል 7,170 እንዲሁም በአፋር ክልል 497 በድምሩ 7,667 ደንበኞች ያለቅጣት ለ6 ወራት በማራዘም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የንግድ ድርጅቶች በፌደራል ደረጃ በተሰጣቸው የንግድ ሥራ ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ በ972 የንግድ ድርጅቶች ላይ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሥራ ለማካሄድ ታቅዶ በ792 (81.5 %) የንግድ ድርጅቶች ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረትየክትትልና የቁጥጥር ሥራ  ከተካሄደባቸው ድርጅቶች መካከል 701 ድርጅቶች በህግ

አግባብ እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የህግ ጥሰት በተገኘባቸው 91(11.5%) ድርጅቶች ከተሰጡባቸው የንግድ ስራ ፈቃድ መስኮችና አላማዎች ውጭ መነገድ ወይም መስራት፣ ባስመዘገቡት አድራሻ አለመገኘት፣ ባልታደሰ ንግድ ፈቃድ መስራት እና የቅርጫፍ አድራሻ አለማስመዝገብ የመሳሰሉ የህግ ጥሰቶችን ፈጽመው በተገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ፈቃዳቸውን በማገድ በመመሪያው መሰረት የታየባቸውን ግድፈት እንዲያስተካክሉ በማድረግ አስተካክለው የቀረቡ ድርጅቶች የተጣለባቸው እግድ እንዲነሳላቸው የማድረግና እንደጥፋታቸው ደረጃም አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን በሚያባብሱ 103,901 ህገወጦች ላይ በየደረጃው በተዋቀረው የዋጋ ማረጋጋት፣ህገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር ግብረ-ሀይል በተደረገ ክትትል ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን በሚያባብሱ ድርጅቶች ላይ በየደረጃው በተዋቀረው ግብረ ሀይል ገበያውን ለማረጋጋት ሲባል በተሰራው ሥራ በአጠቃላይ ብር 7.77 ሚሊዮን በላይ በገንዘብ ከተቀጡ ነጋዴዎች ላይ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

### 2.2.2 መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦትና ስርጭትን በመከታተል የገበያ መረጋጋትን ማረጋገጥ

በኮቪድ 19-ወረርሽኝ ምክንያት በዓለም አቀፍ ደረጃ የምርትና አገልግሎት መቀነስ የፈጠረው የሸቀጦች ዋጋ መናር፣የብር የመግዛት አቅም መዳከም እና በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ችግር ያጋጠመ ቢሆንም ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግስት የውጭ ምንዛሬ በመመደብ እና በአምራች ኢንዱስትሪዎች ድፍድፍ ዘይት እንዲቀርብ በማድረግ ከ103.49 ሚሊዮን ሊትር ዘይት በላይ በአገር ውስጥ ተመርቶ ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ይህም በ8 ወራት መቅረብ ካለበት 320 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር 32.4 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የመሰረታዊ ሸቀጦች ዋጋ ከፍተኛ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም መንግሥት የስንዴ ፍላጎት ጉድለትን ለመሙላት ግዥ ከተፈጸመው 4 ሚሊዮን ኩንታል ውስጥ 1.5 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማሰራጨት ታቅዶ 670,409 (75%) ኩንታል ስንዴ በተቀመጠው የአሰራር ሥርዓት መሰረት ለጸጥታ አካላትና ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

ከስኳር አቅርቦትና ስርጭት ጋር በተያያዘ ባለፉት 8 ወራት ከ1.44 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስኳር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህም ከሀገራዊ ፍላጎት አንጻር 42.4 በመቶ ይሸፍናል፡፡ለአቅርቦት አፈጻጸም ማነስ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመሰረታዊ ሸቀጦች ዋጋ መናር፣የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እጥረት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

መንግሥት በቀጥታ የውጭ ምንዛሬ በመመደብ ከሚያቀርባቸው የመሰረታዊ ሸቀጦች በተጨማሪ በፍራንኮቫሉታ እና በዲያስፖራ አካውንት ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ በፈቀደው መሰረት 481 ሚሊዮን ሊትር ዘይት፣ 8.37 ሚሊዮን ኩ/ል ስኳር፣ 4.98 ሚሊዮን ኩ/ል ሩዝ፣ 687,534 ኩ/ል ፓስታ እና ማካሮኒ፣ ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በመቅረቡ በወቅቱ የነበረውን የሸቀጦችን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን በሚያባብሱ 103,901 ህገወጦች ላይ በየደረጃው በተዋቀረው የዋጋ ማረጋጋት፣ ህገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር ግብረ-ሀይል በተደረገው ክትትል ህጋዊና አሰተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 2.2.3 የአክስዮን፣ ንግድና ዘርፍ ማህበራትና ምክር ቤቶችን ከማጠናከር አንጻር

የአክስዮን፣ ንግድና ዘርፍ ማህበራትና ምክር ቤቶችን ከማጠናከር አንጻር ከአክስዮን ማህበራት ጋር ተያይዞ ለ109 የተለየዩ አካላት መረጃ ፈላጊዎች መረጃ ለመስጠት ታቅዶ 104 (95.4%)፣ ከአክሲዮን አደረጃጀትና አሰራር ጋር ተያይዞ 125 መረጃ ለሚፈልጉ የተለያዩ አካላት መረጃ ለመስጠት ለ120 (96%) ፣ ከንግድና ዘርፍ ሚህበራት ጋር ተያይዞ ለ98 መረጃ ፈላጊዎች መረጃ ለመስጠት ታቅዶ 97 (98.9%)፣ ለነባር የዘርፍና የሙያ ማህበራት 4 የፈቃድ እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ5 (125%) ፈቃድና እድሳት ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም 3 አዲስ የዘርፍና የሙያ ማህበራትን ለማደራጀት ታቅዶ 2 (67%) የዘርፍና የሙያ ማህበራትን የማደራጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የአክሲዮን ማህበራት ከተቋቋሙ በኋላ በንግድ ህጉ፣ በመመስረቻ ጽሁፉና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ስራቸውን እየሰሩ ስለመሆኑ ከመከታተልና ከመደገፍ አኳያ በ21 የአክሲዮን ማህበራት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ27 ማህበራት ላይ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የግል ዘርፍ በኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ተገቢ ሚናውን እንዲጫወት ለማስቻል የንግድ ዘርፍ ማህበራትን ከመደገፍ አኳያ  የአክሲዮን ማህበራት ጉባኤ ሲጠሩ በሕጉ መሰረት ጉባኤው እንዲከናወን በጉባኤው ላይ ተገኝቶ ከጉባዔው ጥሪ ጀምሮ እስከ ጉባዔው ክንውን ድረስ በ25

የአክሲዮን ማህበራት የማማከር፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 20 የአክሲዮን ማህበራት ጉባኤ ላይ በመገኘት ከጉበዔው ምስረታ ጀምሮ የማማከር፣ የመደገፍና የመከታተል ተግባራት ተከናውኗል፡፡

የዘርፍ እና አክሲዮን ማህበራት ከመደገፍ አንጻር አክሲዮን ለህዝብ በመሸጥ የሚቋቋሙ አክሲዮን ማህበራት አክሲዮን ከመሸጣቸው በፊት በህጉ መሰረት የተዘጋጀ መግለጫ መኖሩን በማረጋገጥ በማስታወቂያ ማስነገር እንዲችሉ ፈቃድ ለመስጠት፣አክሲዮን ማህበራት ከተቋቋሙ በኋላም በንግድ ሕጉ፣ በመመስረቻ ፅሁፍና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት ሥራቸውን እያከናወኑ ስለመሆኑ፣በአክሲዮን ማህበራት የቦርድ አመራር፣ በባለአክሲዮኖች እና በማኔጅመንት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሕግ አግባብ እንዲፈቱ፣ በወቅቱ ጠቅላላ ጉባኤ የማይጠሩ አክሲዮን ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠሩ የማማከር፣ የመደገፍና ክትትል የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፡፡

### 2.2.4 ከንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አኳያ

ከሀገር ውስጥ የሚቀርቡ የውህደት ማስታወቂያዎች ጋር በተያያዘ 39 የሀገር ውስጥ የውህደት ጉዳዮች ቀርበው በሁሉም ላይ ሰነድ በማደራጀት፣ በማጣራትና ምርመራ በማድረግ በተለያየ የንግድ ዘርፍ ማለትም በቴክኖሎጂ፣ በጤና አገልግሎት፣ በኮንስትራክሽን፣በግብርና እና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ በአጠቃላይ ከብር 3.18 ቢሊዮን ካፒታል በላይ ካስመዘገቡ ድርጅቶች ውስጥ ከብር 1.08 ቢሊዮን በላይ የሚሆን የውህደትና የአክሲዮን ሽያጭ /ዝውውር/ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የድንበር ተሻጋሪ የውህደት ማስታወቂያዎችን በተመለከተ 8 የድንበር ተሻጋሪ የውህደት ጉዳዮች ቀርበው ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በአጠቃላይ ያስመዘገቡት ካፒታል ከብር 23.41 ቢሊዮን በላይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የብር 76.936 ሚሊዮን የውህደትና የአክሲዮን ሽያጭ /ዝውውር/ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ከኮሜሳ ጋርም በተያያዘ ለመጡ 7 የውህደት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት የተቻለ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ በቅርንጫፍ መስሪያ ቤታቸው እና ምርታቸውን በሚቀበሉ ድርጅቶች አማካኝነት ከ252.580 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ መጠን ያለው ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፀረ ውድድር የንግድ አሠራሮችን በተመለከተ በበላይነት የተያዙ ገበያዎችንን አላግባብ በመጠቀም ተግባር የሚመለከቱ የፀረ- ዉድድር የንግድ ተግባራት፣የፀረ-ዉድድር የንግድ ስምምነት የንግድ ተግባርራትን በፈጸሙ፣ ተገቢ ያልሆነ ንግድ ውድድር ተግባራት በቀረቡ ጥቆማዎች ላይ

አስፈላጊውን ምርመራና ማጣራት በማድረግ በተወሰደው እርምጃ በአጠቃላይ ከብር 1.468 ሚሊዮን በላይ የቅጣት ገንዘብ በመሰብሰብ ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ ንግድ ውድድር በመፈፀም ጥፋተኛ በተባሉ ህገወጥ ነጋዴዎች ላይ ከብር 25.42 ሚሊዮን በላይ የአፈጻጸም ክስ እንዲመሠረት በማድረግ ክርክር እየተደረገ ይገኛል፡፡

የሸማቾችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅም በኢትዮ F.M.፣ በሸገር 102.1 እና በአሃዱ ራዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መዝናኛ እና በቃና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሚተላለፉ የንግድ ማስታወቂያዎች ላይ በተደረገዉ ክትትከል በ3 የንግድ ድርጅቶች ሲነገር የነበረዉ የዋጋ ቅናሽ ማስታወቂያ አሳሳች ይዘት ያለው መሆኑ ስለተረጋገጠ ከንግድ ድርጅቶቹ ጋር በመነጋገር እንዲያስተካክሉ ተደርጓል፡፡

የእርቅና ድርድር ስራዎች ጋር በተያያዘ ከብር 2.02 ሚሊዮን በላይ የያዙ 18 አቤቱታዎች መካከል ከብር 1.99 ሚሊዮን በላይ የያዙ 16 አቤቱታዎች በእርቅና ድርድር አሠራር በስምምነት እንዲያልቁ ሲደረግ ቀሪ 2 አቤቱታዎች ባለጉዳዮቹ ሳይስማሙ ተለያይተዋል፡፡

## 2.3 የወጪ ንግድ ማስፋፋት

### 2.3.1 የኤክስፖርት ምርቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ማሳደግ፣

የወጪ ንግድ ገቢን ከማሳደግ አኳያ ባለፉት 7 ወራት በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣በማዕድን 2.353 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለመግኘት ታቅዶ 2.166 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር (92%) ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ከተገኘው 1.812 ቢሊዮን ዶላር ጋር ሲነጻጸር በ353.5 ሚሊዮን ዶላር (19.5%) ጭማሪ አሳይቷል፡፡

አጠቃላይ ከተገኘው ገቢ ውስጥ በዘርፍ ሲታይ የግብርና ዘርፍ 1.51 (108%) ፣ የኢንዱስትሪ/ ማኑፋክቸሪንግ/ዘርፍ 278 (86.7%) ሚሊዮን ድርሻ በመያዝ ከፍተኛ አፈጻጸም ሲያስመዘግቡ የማዕድን ዘርፍ 322 (56%) ሚሊዮን አፈጻጸም እንዲሁም የኤሌክትሪክ እና ሌሎች የወጪ ምርቶች 56 ሚሊዮን አስመዝግበዋል፡፡ ከግብርና ዘርፍ ውስጥ በገቢ ቡና (30%)፣ አበባ (13%)፣ ጫት (11%)፣ የቅባት እህሎች (7%) እንዲሁም የጥራጥሬ ሰብሎች (5%) ድርሻ ሲኖራቸው ከማዕድን ዘርፍ ደግሞ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት (5%)፣ ስጋና የወተት ተዋጥጻኦ (3%)፣ምግብ፣

መጠጥና ፋርማትካልስ (3%)፣ቆዳና የቆዳ ውጤቶች (1%) እና ብረታ ብረትና ኢንጂነሪግ (0.6%) አፈጻጸም አስመዝግበዋል።

ወደ ውጭ ሀገራት የሚላኩ የወጪ የግብርና ምርቶች ከኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት በተጨማሪ በተቀባይ ሀገራት መስፈርት መሰረት ላኪዎች የሽያጭ ኮንትራት ስምምነት መስፈርትን አሟልተው እንዲልኩ ቁጥጥር መደረጉ፤ ላኪ ድርጅቶች በወቅቱ ኮንትራት እንዲገባ መደረጉ፤ በውል እና በኢንቨስትመንት እርሻ ያለሙ አልሚዎች ምርታቸውን ወደ ዉጪ መላክ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ፤ ከቡና ልማት እስከ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ድረስ የቡና ማምረት፣ መሰብሰብና ማዘጋጀት ላይ ተከታታይ የድጋፍና ክትትል በመሰራቱ፤አዳዲስ ምርቶች ወደ ግብይት ሥርዓቱ እንዲገቡ መደረጉ እና የቡና ጥራት በማሻሻል የምርት አቅርቦቱ እንዲጨምር መደረጉ ለአፈጻጸም መጨመር በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚከታተላቸው የወጪ ምርቶች የ2014 በጀት አመት ሰባት ወራት እቅድ አፈፃፀም

(መጠን በቶን /ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር)

| ተ.ቁ | የወጪ ንግድ ምርት | የ2014 በጀት ዓመት የሰባት ወራት ዕቅድ | | የ2014 በጀት ዓመት የሰባት ወራት ክንውን | | ዕቅድ አፈፃፀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መጠን | ገቢ | መጠን | ገቢ | መጠን | ገቢ |
| 1 | የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚ/ር ክትትል የሚያደርግባቸው ምርቶች | 367,423.40 | 587.1 | 257,199.46 | 509.897 | 70.00 | 86.85 |
| 1.1 | የቅባት እህሎች | 125,933.50 | 179.98 | 105,536.08 | 161.171 | 83.80 | 89.55 |
| 1.2 | የጥራጥሬ ሰብሎች | 183,676.50 | 154.590 | 104,346.27 | 113.950 | 56.81 | 73.71 |
| 1.3 | የተፈጥሮ ሙጫና ዕጣን | 645.00 | 3.009 | 447.53 | 1.924 | 69.38 | 63.92 |
| 1.4 | ጫት | 43,583.60 | 246.365 | 39,290.33 | 231.0 | 90.15 | 93.79 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.5 | ባህር ዛፍ | 12,142.60 | 1.403 | 4,847.66 | 0.778 | 39.92 | 55.43 |
| 1.6 | የብዕርና አገዳ እህሎች | 1,442.20 | 1.764 | 2,731.58 | 0.996 | 189.40 | 56.51 |
| ጠቅላላ ድምር | | 367,423.40 | 587.1 | 257,199.46 | 509.897 | 70.00 | 86.85 |

ከላይ በሰንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚከታተላቸው የኤክስፖርት ምርቶች አፈጻጸም በተመለከተ በ7 ወራት ውስጥ በአጠቃላይ 367,423.40 ቶን የተለያዩ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 587.1ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 257,199.46 (70%) ቶን ምርት በመላክ 509.897 (86.85%) ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በገቢ ጫት (94%)፣የቅባት እህሎች (89.5%) እና የጥራጥሬ ሰብሎች (74%) አፈጻጸም ሲኖራቸው በቁም እንስሳት (42%) አፈጻጸም ተመዝግቧል።

በቻይና መንግስት የወጣው የኤክስፖርት አፈፃፀም ከታህሳስ  ወር ጀምሮ ወደ ቻይና ሃገር ለመላክ በቅድሚያ መመዝገብ ያለበት መሆኑና ለዚህም መለያ ቁጥር እንዲኖር የሚያስገድድ ቢሆንም ለዚህ ስራ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ባለመደረጉ ወደ ቻይና የሚልኩ ላኪ ድርጅቶች ምርታቸውን በወቅቱ ባለመላካቸው በተለይም በጥር ወር ወደ ቻይና የተላከው የሰሊጥ ምርት ካለፈው በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን የ3,477 (74%) ቶን  እና  በገቢ ደግሞ የ5.33 (73%) ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ቅናሽ አሳይቷል። በተጨማሪም ሰሊጥ በከፈተኛ ደረጃ የሚመረትባቸዉ የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና እና ሁመራ በተፈጠረዉ የጸጥታ ችግር ምክንያት በቂ የሆነ የሰሊጥ ምርት ባለመመረቱ በኤክስፖርት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

የቀይ ቦሎቄ እና የቀይ ዥንጉርጉር ቦሎቄ ምርቶች የአለም አቀፍ የገበያ ፍላጎት እና ዋጋ የተቀዛቀዘ መሆኑን ተከትሎ በኤክስፖርት እቅድ አፈፃጸም ላይ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በተጨማሪ

በአልም አቀፍ ገበያ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸዉ አስገዳጅ የሆኑ የኤክስፖርት ምርቶች  እንደ ነጭ ቦሎቄ፣ሰሊጥ፣አኩሪ አተር እና የማሾ ምርቶች  በምርት አቅርቦት እጥረት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ በወቅቱ ባለመቅረባቸው ለኤክስፖርት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል በሚያደርግባቸው የወጪ ምርቶች የቦሎቄ ምርቶች በተለይም ነጭ ቦሎቄ፤ የቀይ ቦሎቄ እና የቀይ ዝንጉርጉር ቦሎቄ ምርት የአለም አቀፍ የገበያ ፍላጎት መቀዛቀዝ እና ዋጋ መቀነስ ምክንያት ከወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ አፈፃፀም ዝቅ እንዲል ቢያደርገውም በወቅቱ ለወጪ ገበያ እንዲቀርብ  በተገኘ ገበያ ዋጋ መሰረት መላክ እንዲችሉ አስተዳደራዊ መፍትሄ እንዲያገኝ  ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የጫት ምርት አቅርቦት እጥረት ጋር በተያያዘ በኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት በህግ ወጥ የሚባክነዉን የጫት ምርት ለመከላከል  ከባለድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት  ክትትልና ቁጥጥር እተደረገ ይገኛል፡፡

ባለፉት ሰባት ወራት የቅባት እህሎች፤ የጥራጥሬ ሰብሎች እና የጫት ምርት የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ለማሳደግ  በተሰራው ሥራ  የወጪ ምርት ከፍተኛ እምራች የሆኑ አካባቢዎች በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንድያቀርቡ የተቀናጀ የክትትልና ድጋፍ ስራ 99,751 ቶን የሰሊጥ እና 63,997 ቶን የጥራጥሬ ምርት በድምሩ 16,3748  ቶን ምርት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንዲቀርብ በማድረግ 98,421.1 ቶን  የሰሊጥ እና 60,519.2 ቶን በድምሩ 158,940.3 ቶን የጥራጥሬ ምርቶችን ላኪ ድርጅቶች ግብይት እንዲፈፅሙ አስችሏል፡፡

በክምችት የነበረ የቀይ ቦሎቄ ምርት የዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ ፍላጎት በመቀዛቀዙ እና የገበያ ዋጋዉ በመቀነሱ ምክንያት መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን በአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ መሰረት የዋጋ መስተካከያ የዉሳኔ ሀሳብ በማቅረብ  መፍትሄ እንዲያገኝ የማድረግ ስራ ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም በክምችት የነበረ የቀይ ቦሎቄ ምርት የዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ ፍላጎት በመቀዛቀዙ እና የገበያ ዋጋዉ በመቀነሱ ምክንያት መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን በአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ መሰረት የዋጋ መስተካከያ የዉሳኔ ሀሳብ በማቅረብ  መፍትሄ እንዲያገኝ የማድረግ ስራ ተከናዉኗል፡፡

በዉል እና በኢንቨስትመነት እርሻ ያለሙ አልሚዎችን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት መረጃዉን በመተንተን እና በማደራጀት የተመረተዉን ምርት በወቅቱ ኮንትራት ገብተዉ ወደ ዉጪ መላክ እንዲችሉ የማጣራት ስራ ተከናዉኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባንክ መላኪያ ፍቃድ ላላቸዉ ላኪ

ድርጅቶች ምርታቸዉን ወደ ዉጪ መላክ እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 43.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተምዝግቧል።

ከአለም አቀፍ ገበያ በታች የሚደረገው ሽያጭ /under invoice/ ለመከላከል የኑግ፣የባቄላ፣ የሽምብራ፣ የጓያ፣ የለውዝ፣ የግብጦ ምርቶችን በውል ምዝገባና አፈጻጸም ሥርዓት ዉስጥ በማከተት በየሳምንቱ አለም አቀፍ የማነፃፀሪያ ዋጋ በማዉጣት በተደረገው የማስተካከል ሥራ ተጨማሪ 3.74 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን የተለያዩ ጥራጥሬ ምርቶች እና የቅባት እህሎች ኮንትራት እንዲመዘገብም ተደርጓል ።

በ84 ላኪ ድርጅቶች ላይ በተደረገዉ ክትትል 12,607 ቶን የሰሊጥ እህል እና 36,623 ቶን የጥራጥሬ ምርት በድምሩ 49,230 ቶን ምርት በላኪዎች መጋዘን በክምችት እንደሚገኝ የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይ ወደ ገበያ እንዲያወጣ የማድረግ ሥራ የሚሰራ ይሆናል።

### 2.3.2 የገበያ ፕሮሞሽንና ትስስር ሥራዎችን ከማከናወን አንጻር

የወጪ ንግድ ገቢያችንን ለማሳደግ በዓለም ዓቀፍ የንግድ ትርዒቶች ላይ የወጪ ምርቶቻችን በማስተዋወቅና ላኪዎቻችን የገበያ ትስስር በመፍጠር ምርቶቻችንን በተሻለ ዋጋ እንዲሸጡ ለማድረግ በተሰራው ሰፊ ሥራ በዱባይ ከተማ በተደረገው የምግብ የንግድ ትርዒት ላይ ከ200 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ጎብኝዎች ሀገራችን ለዓለም አቀፍ ገበያ የምታቀርባቸውን የተለያዩ ምርቶች በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ የተሰራ ተሰርቷል።

በአጠቃላይ ከ107 ላኪ ድርጅቶች የተውጣቱ 145 ተሳታፊዎች በንግድ ትርዒት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ከተቀባይ ኩባንዎች ጋር በተደረገው የገበያ ትስስር የጥራጥሬ ሰብሎች 13,848 ቶን ምርት ግምቱ 14.92 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣የቅባት እህሎች 4,1426 ቶን ግምቱ 6.89 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ቅመማ ቅመም 123 ቶን ምርት ግምቱ 253,990 የአሜሪካን ዶላር፣ ቡና 2,800 ቶን ግምቱ 9.39 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ሥጋ 2,250 ቶን ግምቱ 14.74 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሁም ማር 20 ቶን ግምቱ 70 ሺህ የአሜሪካን ዶላር በድምሩ 60,467 ቶን ምርት ግምቱ 46.26 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሊያወጣ የሚችል የኮንትራት ውል እንዲገባ ተደርጓል። ይህ አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ከተገኘው 44.57 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጋር ሲነጻጸር በ1.69 (3.79%) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ አሳይቷል።

የንግድ ትርዒቱን ከጎበኙት የተለያዩ አገራት ገዥዎች መካከል የሀገራችንን የወጪ ምርቶች ለመግዛት፣ በሀገራችን ያሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በመጠቀም ለማልማት እና ከ3,800

በላይ የሚሆኑ ጎብኝዎች ወደ ሀገራችን ለመምጣት ፍላጎት ያላቸው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ምርቶቻቸውን ወደ ሀገራችን ለመላክና በቀጣይም በሀገራችን ለማምረት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በናይጄሪያ 'Food and Beverage West Africa' ዓለም ዓቀፍ የምግብ ኤግዚቢሽን ላይ የገበያ ፕሮሞሽና ትስስር ሥራዎች በማስራት ሀገራችን ከአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ተጠቃሚ እንድትሆን ለማስቻል በተሰራው ሥራ በኤግዚቢሽኑ ከቀረቡት የግብርና ምርቶች መካከል ከ3 ድርጅቶች ጋር በእንስሳት ተረፈ ምርት የኮንትራት ውል እንዲፈጽሙ ተደርጓል፡፡

እ.አ.አ ከመስከረም 5-6 2021 በአሜሪካ ሀገር በተካሄደው Ethio-US ዓለም ዓቀፍ የንግድ ትርዒት እና ከየካቲት 13-17 2022 በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ዱባይ ከተማ በተካሄደው ገልፍ ፉድ 2022 ዓለም ዓቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ተሳትፎ ላደረጉ 64 የሀገራችን ላኪዎች የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ ቅመም እና ማር ምርቶችን ወደ ዱባይ ይዘዉ በመሄድ እንዲያስተዋውቁ እና የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ የናሙና ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

### 2.3.3 የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮችን በማካሄድ የመዳረሻ ገበያዎችን ማስፋት

የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮችን በማካሄድ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማስፋት በኢትዮ-ኬንያ የተቀላጠፍ የጠረፍ ንግድ ስምምነትን ረቂቅን/Simplified Border Trade Agreement/ ላይ ረቂቅ ስምምነት ተዘጋጅቶ እና ለንግድ የሚሆኑ ምርቶች ተለይተው ከኪንያ ወገን ድርድር የተደረገ ሲሆን በድርድሩ ተጨማሪ ምርቶች የማካተተት እና በስምምነቱ የተወሰነ ክፍሎች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም 27ኛው የኢትዮ-ጂቡቲ የጋራ ድንበር አስተዳዳሪዎች የድርድር ሰነድ ተዘጋጅቶ ውይይት ተደረገ ሲሆን በጠረፍ አካባቢ ከንግድ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ለመፍታት ስምምነት ተደርሷል፡፡ በኢትዮ-ፓኪስታን እና የኢትዮጵያና የተባበሩት አረብ ኤምሬት ረቂቅ የንግድ ስምምነት ተዘጋጅቶ ለፓኪስታን እና የተባበሩት አርብ ኤምሪትስ በዲፕሎማሲ መስመር እንዲደርስ ተደረጓል፡፡

ሀገራችን ከ7 ሀገራት (ቻይና፣ አልጀሪያ፣ ኬንያ፣ ህንድ፣ ራሽያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬት እና ሩዋንዳ) ጋር ያለውን የንግድ ግንኙነት የሚመለከት ሰነድ/Countries' Profile/ በማዘጋጀት ለቀጣይ ድርድሮች ዝግጁ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፡፡ የጫት ወጪ ንግድ በተመለከተ የጥናት ሰነድ እና የድርጊት መርሀግብር ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በጥናቱ መሰረት ከሀገራችን ወደ ሶማሊያ

የሚላከው ጫት ከአምስት ዶላር ወደ አስር ዶላር ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ በጠረፍ  አካባቢ ላሉ የነጋዴዎች ማህበራት አመራሮች፣ የወረዳና ዞን ንግድ ጽ/ቤት እና የክልል ንግድ ቢሮ ባለሞያዎች በጠረፍ ንግድ መመሪያ እና በህጋዊ ንግድ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡

### 2.3.4 የአካባቢያዊ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ስራዎችን በማጠናቀቅ ወደ ትግበራ ከማስገባት አንጻር

የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ጋር በተያያዘ የእቃዎች ንግድ ኦፈር በ2017 በተሻሻለው የታሪፍ መጽሐፍ እና ከ2022 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሚሆነው የታሪፍ መስመር መሰረት በቅድሚያ ማለትም በ10 አመታት ውስጥ ሊበራላይዝ የሚደረጉ ፣ በረጅም ጊዜ ማለትም በአስራ ሶስት አመታት ውስጥ ሊበራላይዝ የሚደረጉ እና ሊቢራላይዝ የማይደረጉ ምርቶች ላይ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት፣ ከግሉ ማህበረሰብ እና ከሙሁራን ጋር በመወያየት ምርቶችን የመለየት ስራ ተጠናቋል፡፡ በተጨማሪም በአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና በሚካሄዱ ድርድሮችን በሚኒስትር፣ በሲኒየር ኦፊሻል እና በኤክስፐርቶች ደረጃ የሚደረጉ ድርድሮች ላይ በመሳተፍ የሀገራችን አቋም ለማነጸባርቅ ተችሏል፡፡

በሌላም በኩል በኢጋድ ድጋፍና ትብብር የአፍሪካ ነጻ አህጉራዊ ንግድ ቀጣና የትግበራ ስትራቴጂ በቁም እንሰሳት፣ የሰብል እህሎች እና የቆዳ ውጤቶች ላይ ያተኮረ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የስራት ሀገር ምንጭ፣የጉምሩክ ትብብርና አስተዳደር እና ትራንዚት ንኡስ ኮሚቴ እንዲሁም የንግድ ማሳለጥ እና National Committee for Non-tariff Barriers to Trade ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

የምስራቅና ደብባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ(ኮሜሳ) በተመለከተ የኮሜሳ የአባልነት ተሳትፎ ከአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ምስረታ ያለው አንድምታ የሚሳይ ቢጋር ተዘጋጅቷል፡በኮሜሳ ጉዳዮች ላይ በሚካሄዱ ድርድሮች ላይ በመሳተፍ የሀገራችን አቋም ለማነጸባርቅ ተችሏል፡፡ በኮሜሳ EDF 11 ፕሮጀክትን ለማስፈጸም እንዲቻል የቴክኒክ ኮሚቴውን መምራት እና የማስተባበር የተመደበውን በጀት በመጠቀም የጋላፊ አንድ አለቅ የድንበር አገልግለት (One Stop Border Post /OSBP/)፣ ለጉምሩክ ኮሚሽን እና ለአንድ መስኮት አገልግሎት ጽ/ቤት ለሚገዙ የሰርቨር እና ስቶሬጅ ድጋፍ እና በጠረፍ አካባቢ ለሚኖሩ የንግድ ማህበረሰብ የገበያ ማዕከል እንዲገነባላቸው የጨረታ ሂደቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

### 2.3.5 የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድርን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ፡

የዓለም ንግድ ድርጅት በአባልነት የዕቃዎች ኦፈር ጥያቄዎች ምላሽ ማዘጋጀትን በተመለከተ በታይላንድና በካናዳ ለተጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ተዘጋጅተዋል፡፡ የእቃዎች የገበያ እድል ሰነድ የመከለስ ስራ ተከናውኗል፡፡በቅርቡ የዓለም ንግድ ድርጅትን የተቀላቀሉ የ36 አገራት በአእምሮአዊ ስምምነት የገቡት ግዴታ የሚሣይ ሰነድ የማደረጃት ስራ ተከናውኗል፡፡የሀገር ውስጥ የግብርና ድጋፍና ኤክስፖርት ድጎማ ከ2019/20 እስከ 2021/22 ከገንዘብ ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሠረት የተደረጀ ሲሆን በቅርብ ጊዜ የአለም ንግድ ድርጅት የተቀላቀሉ የስድስት ሀገራት (የአፍጋንስታን ፣የላይቤሪያ፣ የቫኑዋቱ፣ የላኦስ ፣የሳሞአ እና የየመን)፤ በግብርና የወሰዱት ግዴታ ሰነድ እንደ ግብአት ለመጠቀም ተችሏል፡፡

የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድርን የሚረዱ ሰነዶችን ከማዘጋጀት አንጻር አጠቃላይ የኢትዮጵያ አገልግሎት ዘርፍ እና የአገልግሎት ንግድ ዳሰሳ ጥናት በረቂቅ ደረጃ ተከናውኗል፡፡ የአገልግሎት ንግድ ኢንኮየሪ ፖይንት ለማቋቋም የሚረዳ የተዘጋጀው ሰነድ የመከለስ ስራ ተከናውኗል፡፡ የእጽዋት፣ የእንሳሳት እና የሰው ጤና (Sanitary and phyto sanitary, SPS) 16 የሚሆኑ የስምምነቱ አንቀፆች ወደ አማርኛ የመተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡

### 2.3.6 የገበያ ጥናትና ማስፋፊያ ሥራዎችን ከማጠናከር አኳያ (የቁም እንስሳትና ቆዳና ሌጦ)

የቁም እንስሳት የገበያ መረጃን ለማጠናከር 27 የገበያ መረጃ የሚሰበሰብባቸውን ማዕከላት ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በሶስት ክልል ማለትም በሶማሌ፣ በኦሮሚያና ደቡብ 17 የገበያ ማዕከላትን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በየደረጃው ማለትም ከክልል ጀምሮ እስከ ገበያ ማዕከል ድረስ ግብረ መልስ ተልኳል፡፡ በተመረጡ 56 የገበያ ማዕከል በ5 ክልሎችና በ2 የከተማ አስተዳደሮች ስልጠና በመስጠት ወደ ዳታ ቤዝ እንዲያስገቡ በተያዘው እቅድ መሰረት 47 የገበያ ማዕከላት በተዘጋጀው ዳታ ቤዝ ሪፖርት እየላኩ ይገኛሉ፡፡

ከቁም እንስሳት የሚገኘውን የውጪ ምንዛሩ ግኝት ለማሳደግ 29,653 የዳልጋ ከብቶችን ወደ ውጭ በመላክ 19.148 ሚልዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 11,159 የዳልጋ ከብቶችን ወደ ውጭ በመላክ 5.912 (30.88%) ሚልዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 163,198 በግና ፍየል ወደ ውጭ በመላክ 11.54 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 4,340 በግና ፍየል ወደ ውጭ በመላክ 0.177 (1.33%) ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡በተመሳሳይ 21,421 ግመል ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 17.31 ሚልዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 11,763 ግመል ወደ ውጭ በመላክ 5.4(31.2%) ሚልዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

በጠቅላላው በሰባት ወራት 214,272 የቁም እንስሳትን ወደ ውጭ በመላክ 48.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ታቅዶ 27,262 (የ12.72) ቁም እንስሳትን ወደ ውጭ በመላክ 11.866 (24.67) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

ዘመናዊ የቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓትን በመዘርጋት የግብይት ስርዓትን ለማዘመን በተሰራው ሥራ 1,041,667 የበሬ ቆዳ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 335,500 (32.2%) ቀርቧል፡፡ 3,416,667 የበግ ሌጦ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 3,038,000 (88.9%) ለገበያ ቀርቧል፡፡ 2,541,667 የፍየል ሌጦ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 749,762 (29.5%) ለገበያ ቀርቧል፡፡ በአጠቃላይ 7,000,001 የቆዳና ሌጦ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 4,123,262 (58.9%) ለገበያ ቀርቧል፡፡

ህገወጥ የቁም እንስሳት ግብይትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከክልሎችና ከላኪዎች እንዲሁም ከአዳማ ከተማ ንግድና ገበያ ልማት መምሪያ፣ ከኳራንቲን ጣቢያ ሀላፊዎች ፣ አድላቢዎችና ላኪዎች ጋር በተደረገው ምክክር በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ ከተያዙ 364 የቁም እንስሳቶች 198 የቁም እንስሳት ባለቤት ነን ባዮች ህጋዊ መረጃ በማቅረባቸው እንዲለቀቁ የተደረገ ሲሆን 161 የቁም እንስሳት ህጋዊ ማስረጃ ሊቀርብባቸው ባለመቻሉ እንዲወረሱ በማድረግ በውሱን ጨረታ እንዲሸጡ ተደርጓል፡፡ ከቁም እንስሳት ጋር ተያይዞ የሚታየውን የትራንስፖርት ችግሮች ለመፍታት ከትራንስፖርት ሚኒስቴርና ከላኪዎች ጋር የጋራ ምክክር ተደርጓል፡፡

ከቁም እንስሳት የሚገኘው የወጪ ገቢ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ የሆነበት ምክንያት የኮትሮባንድ ንግድ በመስፋፋቱ በአቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ ነው፡፡ በሕገወጥ መንገድ ለሚያዙ የቁም እንስሳት በቂ የሆነና የተደራጀ ፋይናንስ አለመኖር የተስተዋለ ችግር ቢሆንም የቁጥጥር ስርዓትና መዘርጋትና ቅንጅታዊ አሰራርና ማጠናከርና በቂ በጀት እንዲመደብ በማድረግ በቀጣይ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫ ምክንያት በማድረግ በቆዳና ሌጦ ከእርድ በፊት፣ በዕርድ ወቅትና ከዕርድ በኋላ በአያያዝና በግብይት ሂደት የግንዛቤ መስጫ በሚዲያ እንዲደርስ በማድረግ የቆዳና ሌጦ ግብይት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እንዲሻሻል አድርጎታል፡፡

ባለፉት ዓመታት የተከሰተውን የኮሮና ወረርሽኝ ተከትሎ የቆዳና ሌጦ የአለም ገበያ መቀዛቀዝ፣ የፍየል ሌጦ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለመኖሩ ምክንያት የቆዳ ፋብሪካዎች ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን እንዲሁም ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ማዛጋጃ የሚሆን ጨው ከኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ

ግብዓቶች ልማት ድርጅት ጋር  በመነጋገር አቅርቦቱ በተሰራው ሥራ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በበቂ ሁኔታ አለመቅረብ ፣የጥራት ቁጥጥሩ ደካማ መሆን፣ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የኤክስቴንሽን ሥራ መዳከም ከኤክስፖርት ሊገኝ የሚችለው ገቢ እንዲቀንስ ምክንያት ሆነዋል፡፡እንዲሁም ከቁም እንስሳት የሚገኘው የወጪ ገቢ አነስተኛ እንዲሆን የኮትሮባንድ ንግድ በመስፋፋቱ በአቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ ነው፡፡

## 2.4 የጥራት መሰረተ ልማት

### 2.4.1 ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶችን በሚያመረቱ 240 ፋብሪካዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ231 (96.25%) ፋብሪካዎች በተደረገው የፊዚካል ምርመራ 204 (88.3) ፋብሪካዎች በተመጠው ደረጃ መስፈርት መሰረት እየሰሩ መሆኑ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን  የፊዚካል ምርመራ ከተደረገባቸው 231 ፋብሪካዎች መካከል ችግር ይኖርባቸዋል ተብሎ በሚገመቱ በ27 ፋብሪካዎች 41 ወካይ ናሙናዎችን በመውሰድ አካላዊ /የፊዚካል/ ምርመራ ተከናውኗል፡፡

በተደረገው የምርመራ ውጤት መሰረት 17 ፋብሪካዎች የምርት ጥራቱ ከደረጃ በታች በመሆናቸው ከማምረት ሂደታቸው እንዲታገዱ በማድረግ እርምጃ ከተወሰደባቸው በኋላ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ማስተካካያ በማድረጋቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

### 2.4.2 ምርቶችን በገበያ ቦታ በመገኙት የኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ሥራዎችን በማካሄድ ጥራታቸው፣ደህንነታቸውና ትክክለኛነታቸውን ማርጋገጥ አኳያ

ባለፉት 8 ወራት በሀገር ውስጥ ተመርተው እና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ተገዝተው የሚገቡ አስገዳጅ በሆኑ በ24 የምርት ዓይነቶች ላይ በገበያ ላይ የኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ሥራ ለማከናውን ታቅዶቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራባቸው በሚገባባቸው 20 (83.4%) የምርት ዓይነቶች ላይ 69 ወካይ ናሙናዎች ከገበያ እና ከማከማቻ መጋዘን ላይ ወካይ ናሙናዎች በመውሰድ በአካለዊ ምርመራና በቤተ-ሙከራ /ላቦራቶሪ/ ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን የማረጋገጥ ስራ በማከናወን 30 ወካይ ናሙናዎች ወይም 17 የምርት ዓይነቶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ ሲሆኑ ጥራታቸውን ባልጠበቁ **39 ወካይ ናሙናዎች** ወይም **18 የምርት ዓይነቶች** የምርት ጥራት ከደረጃ በታች መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም የምግብ ጨው በሚያመርቱ ድርጅቶች ላይ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ጋር በመተባበር በጋራ በተሰራ ሥራ ገበያ ላይ ለህብርተሰቡ እዳይቀርቡና እንዲወገዱ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በዩኒየኖችና በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ላይ በተደረገ ምልከታ 1,309 ኩንታል ጥራቱን ያልጠበቀ የስኳር ምርት በላብራቶሪ ተረጋግጦ ውጤቱ እስኪታውቅ ድረስ ለተጠቃሚ እንዳይቀርብ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶችንና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምርቶች ባቀረቡ ድርጅቶች ላይ 10 ኩንታል በላይ የተለያየ ዓይነት የምግብ ጨው፣የወተት ጣዕም ያለው የማንጎ ጭማቂ፣የእጅ መታጠቢያ ፈሳሽ ሳሙናና ኤሪያል የዱቀት ሳሙና እና የልብስ ሳሙና በተደረገው የጥራት የቁጥጥር ስራ እና ከህብረተሰቡ በደረሰ ጥቆማ ምርቶቹ ገበያ ላይ ቀርበው በህብረተሰቡ ላይ የጤና ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገዱ በማድረግ ሊደርስ የነበረውን የጤንነት ጉዳት በተቻለ መጠን ለመከላከ ተችሏል፡፡

### 2.4.3 የብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትን ከማጠናከር አንጻር

ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ይህን ሊያስፈጽሙ የሚችሉ ተጠሪ ተቋማትን መከታተል፣ መደገፍ እና የማስፈፀም አቅማቸውን በማሳደግ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ በአለም ባንክ የብድር ድጋፍ በሚከናወኑ የፕሮጀክት ስራዎች ላይ ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር አፈጻጸሞችን በጋራ የመገምገም፣ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ በመከታተል የሚስተዋሉ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው አቅጣጫ እንዲሰጥባቸው የማድረግ እና የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ያለበት ደረጃ የመገምግም ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከአለም ባንክ ብድር ፕሮጀክት ጋር በመቀናጀት ከጥራትና ደረጃዎች ክትትልና ቁጥጥር ጋር ግንኙነት ያላቸውን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨምሮ የክልል የሬጉላቶሪ ዘርፍ ኃላፊዎችችና ባለሙያዎችን አቅም ለመገንባት የሚያስችል የስልጠና ዕቅድ እንዲዘጋጅ የማስተባበር፣ የተዘጋጀውን የስልጠና ዕቅድ የመገምገምና የጋራ የማድረግ ስራ የተሰራ ሲሆን በተዘጋጀው የስልጠና ፍላጎትና ዕቅድ አዘገጃጀት ዙሪያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችችና ባለሞያዎች ተግባር ተኮር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ላቦራቶሪና ቢሮዎች ግንባታ ጋር በተያያዘ መንግስት ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ በጀት በመመደብ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት የላቦራቶሪና ቢሮዎች ህንጻ ግንባታ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ክትትል እየተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም 47% ላይ ይገኛል።

ከአለም ባንክ በተገኘ የ50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብድር የተቋማቱ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ግዥና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማጠናከር የተቋማቱን ብቃትና አለምአቀፍ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል። ለፕሮጀክቱ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንዲሟሉ በተቋራጩ ጥያቄ እና በአማካሪ ድርጅቱ ድጋፍ ከ223.12 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ግምት ያላቸው የግንባታ ቁሳቁሶች ከውጭ ተገዝተው እንዲገቡ ለጉምሩክ ኮሚሽን የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጻፍ ተደርጓል።

በግንባታው ዙሪያ የተቋራጩ የረጅም ጊዜ የክፍያ ጥያቄ እና የዋጋና ውል ማስተካከያ ጥያቄ /price adjustement/ ከተለያዩ ክፍሎች የገበያ ጥናት ኮሚቴ በማቋቋም ጥናቱ ተጠናቆ ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረግ የጥናቱን ዉጤት ተከትሎ ከተቋራጩ ጋር ተከታታይ ዉይይት ተደረገ ሲሆን የዋጋ ማስተካከያ፣የዉል መሻሻያ እንዲሁም የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄዎች በዚህ ወር ለመጠናቀቅና የግንባታዉን ስራ ለማስቀጠል እየተሰራ ይገኛል።
ከዚህም በተጨማሪ የቅድመ ክፍያ ዋስትና/Advance payment guarantee/ የዕድሳት ጥያቄው ለሚመለከተዉ ባንክ በመጻፍ ዋስትናዉ እንዲታደስ የማድረግ፣ በተቋራጩ የቀረበ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ 431 ተጨማሪ ቀናት የመስጠት፣ለግንባታ ፕሮጀክቱ ስራ በባለሙያነት እያገለገሉ ለሚገኙ 38 ቻይናውያን የመኖሪያ ፈቃድ፣ የመታወቂያ ዕድሳት እና የስራ ፈቃድ እድሳት እንዲሁም አዲስ ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ የግንባታ ባለሙያ ቻይናውያን የቪዛ ጥያቄ በሚመለከት ለኢሚግሬሽን፣የዜግነትና ወሳን ኩነት ኤጀንሲ እና ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ የመጻፍ ተግባራት ተከናውነዋል።

በአጠቃላይ ከጥራት መሰረተ ልማት የግንባታ ፕሮጀክት ስራ ጋር በተያያዘ በአማካሪ መሃንዲሱ አማካኝነት በግንባታ ሥራው ላይ እየተሳተፉ የሚገኙ 60 ቻይናዉያን ሰራተኞች ስራ ላይ መሆናቸዉን በሳምንታዊ አቴንዳንስ ክትትል እየተደረገ ይገኛል።

### 2.4.4 የሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓትን በማጠናከርና በማዘመን

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል የሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥራ አንዱ ነው። የሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓትን በማጠናከርና በማዘመን የክብደትና የርዝመት፣

የይዘትና የቅደመ እሽግ /Pre-pack/ እና የጤናና ደህንነት ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራዎች ይሰራሉ።ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ የመለኪያ መሳሪያዎች በግብይቱ ውስጥ እንዲገኙ በማስቻል ሸማቹ ህብረተሰብ ለከፈለበት ዋጋ ተመጣጣኝ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኝ እና ፍትሃዊ የንግድ ልውውጥ እንዲሰፍን ለማድረግ ከውጭ ወደ ሀገር ወስጥ የሚገቡ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ልዩ ልዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን እና በግብይት ውስጥ የሚገኙ መሳሪያዎችን የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል።

በዚህም መሰረት 1,127,067 የክብደት ማነፃፀሪያዎችንና ሚዛኖች፣ የርዝመት መለኪያዎችን ፣ የተሽጋጋሪ ሚዛኖችን እና የፈሳሽ መለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት የደንበኞች ጥያቄ ባለመቅረቡ ምክንያት 798,753 (70.9%) ልዩ ልዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን የቬሪቪኬሽን አገልግሎት በመስጠት ማረጋገጥ ተችሏል።

በተጨማሪም የነዳጅ ምርት ብክነትንና ሕገወጥነትን ለመከላከል የፈሳሽ ማጓጓዣ ቦቴዎችን ታንከር ይዘት በመወሰን ህብረተሰቡንና መንግሥትን ተጠቃሚ ለማድረግ 2,005 የፈሳሽ ማጓጓዣ ቦቴዎች ታንከር ይዘት ለመወሰን ታቅዶ በእቅዱ መሰረት የደንበኞች ጥያቄ ባለመቅረቡ 1,611 (80.4%) የፈሳሽ ማጓጓዣ ቦቴዎች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል። እንዲሁም የአውቶ ቦቴ ቬሪፊኬሽን ማዕከል ለማዘመን እንዲቻል ከሚኒስቴር መ/ቤቱና ከብሔራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቋሞ ጥናት ተጠንቶ የጥናት ሰነዱ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን እና የጤናና የደህንነት መለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ታሽገው ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና የሀገር ውስጥ አምራች ድርጅቶች ላይ መረጃ የማሰባሰብና የመለየት ስራዎችን የመስራት፣የቅድመ እሽግ ማከናወኛ የደረጃ መስፈርት ዝግጅት የሚረዱ ረቂቅ መመሪያ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል።

### 2.4.5 የገቢ እና የወጪ ምርቶችን ጥራት ከማረጋገጥ አንጻር

አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው የገቢ ምርቶች ላይ የጥራት ቁጥጥር በማካሄድ የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት ማስተበቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው።

በዚህም መሰረት 1,600,000 ሜትሪክ ቶን የገቢ ምርቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ11,633,026.69 (102%) ሜትሪክ ቶን የገቢ እቃዎች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ

በማከናወን ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ይህ አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወራት ጋር ሲነጻጸር የ8.43% ጭማሪ አሳይቷል፡፡

በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የኢንስፔክሽን ስራዎችን በማከናወን በሀገር ውስጥ ላብራቶሪ መፈተሽ የሚችሉ ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በመላክ እንዲፈተሹ በማድረግ በፍተሻ ውጤቱ መሰረት የኢትዮጵያን ደረጃ ያሟሉ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ከሀገር እንዲወጡ ፍቃድ የተሰጠ ከመሆኑም በላይ የውሃ ፓምፕና የሶላር ቴክኖሎጂ የገቢ ምርቶችን በተመለከተ የሦስተኛ ወገን አለም አቀፍ የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እያቀረቡ እንዲስተናገዱ ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ በ476,000 ሜትሪክ ቶን የወጪ ምርቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተፈጠረው የጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ወደ ሱዳን የሚላኩ የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን የመሳሰሉ የወጪ ምርቶች በመቀነሳቸው 372,132.17 (78.2%) ሜትሪክ ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ፈቃድ የተሰጠ ከመሆኑም በተጨማሪ ወደ ውጭ ሀገራት የሚላኩ የወጪ የግብርና ምርቶች ከኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት በተጨማሪ በተቀባይ ሀገራት መስፈርት መሰረት ላኪዎች የሽያጭ ኮንትራት ስምምነት መስፈርትን አሟልተው እንዲልኩ ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል፡፡

በ2,105,941.66 ሜትሪክ ቶን ልዩ ልዩ የገቢና ወጪ ምርቶች ላይ 7,107 የሚሆኑ የአገልግሎት ጥያቄዎች ቀርበው ሁሉም ጥያቂዎች የተቀመጠውን የጥራት መስፈርት አሟልተው በመገኘታቸው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እና ከሀገር እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ከእነዚህ የገቢና የወጪ ምርቶች ውስጥ 86.5 በመቶ የሚሆውን የሚሸፍኑት ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የምግብ ውጤቶች፣ እንዲሁም ከወጪ ምርቶች ውስጥ 60.23 በመቶ የሚሆውን የሚሸፍኑት የቅባት እህሎች መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡ ከገቢና ከወጪ ምርቶች ጋር በተያያዘ ከሚሰጠው የኢንስፔክሽን እና የሕትመት አገልግሎት ክፍያ ብር 1,650,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 1,589,978.6 (96%) ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት የተለያዩ የገቢ ምርቶች ላይ በተደረገው የላብራቶሪ ፍተሻ እና የኢንስፔክሽን ስራ 908.061 ሜትሪክ ቶን ግምት ያላቸው የገቢ ምርቶች ከደረጃው በታች መሆናቸው በመረጋገጡ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ በማድረግ በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት ከመድረስ በፊት ለመከላከል ጥረት የተደረገ ሲሆን በተመሳሳይም በወጪ ምርቶች በተደረገው የጥራት ቁጥጥር የተለያየ መጠን ያላቸው የወጪ ምርቶች ማለትም አኩሪ አተር፤ ኑግ፣ ጉሎ፤ ሠሊጥ፣ ባቄላ፣ ቦለቄ እና ዥንጉርጉር ቦሎቄ በላቦራቶሪ በተደረገው ፍተሻ የተቀመጠውን የጥራት

መስፈርት ባለማሟላታቸው እንደገና ተበጥረው በImpurity Parameter/ የንጽሕና መለኪያ/ጥራታቸውን ጠብቀው ከሀገር እንዲወጡ በማድረግ የሀገርን ገጽታ ለመገንባትና የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 2.4.6 የሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓትን ከማጠናከርና ከማዘመን አንጻር፤

ከ1.12 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና በገበያ ላይ የሚገኙ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ልዩ ልዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ታቅዶ 798,753 (70.9%) የተከናወነ ሲሆን 2,005 የፈሳሽ ማጓጓዣ ቦቴዎችን ታንከር ይዘት ለማረጋገጥ ታቅዶ 1,611 (80.4%) የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡

ከህጋዊ ስነ-ልክ አገልግሎት አሰጣጥ ክፍያዎች ጋር በተያያዘ ለተሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ከደንበኞች ብር 6,384,720 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 9,282,824.85 (145.39%) ገቢ ተሰብስቦ ወደ መንግስት ግምጃ ቤት ገቢ ሆኗል፡፡

ከስነ-ልክ መሳሪያዎች ጋር በተያያዘ ለ17,745 ልዩ ልዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን የካሊብሬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 14,754 (83%) የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

ዓለም አቀፍ እውቅና በተገኘባቸው በፍተሻ ላቦራቶሪ፣ በሰርተፍኬሽን እና በኢንስፔክሽን የ61 ወሰኖችን እውቅና ማስጠበቅ የተቻለ ሲሆን በፍተሻ ላቦራቶሪ፣በሰርተፍኬሽን እና በኢንስፔክሽን አዲስዓለም አቀፍ እውቅና ለማግኘት በ94 ወሰኖች ላይ ጥያቄ ቀርቦ የሰነድ ግምገማ ተከናውኗል፡፡

በተጨማሪም በፍተሻ ላቦራቶሪ፣በኢንስፔክሽን እና በሰርተፍኬሽን በድምሩ በ41 ወሰኖች ላይ አዲስ አለም አቀፍ እውቅና ለማግኘት የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊና ብሄራዊ ደረጃዎችንና ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ ለጥራት መሰረተ መዋቅሩ የሚያገለግሉ 66 ብሄራዊ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 60 ደረጃዎችን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ለተስማሚነት ምዘና አካላት በአለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ከመስጠት አኳያ ለ6 የሕክምና ላቦራቶሪ፣የፍተሻና የካሌብሬሽን ላቦራቶሪ እና ለኢንስፔክሽን ተቋማት የአክሪዲቴሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

### 2.4.7 የሀገሪቱን አስገዳጅ ደረጃዎች፣የቴክኒክ ደንቦችን በተመለከተ

የሀገሪቱን አስገዳጅ ደረጃዎች፣የቴክኒክ ደንቦችን በተመለከተ 20 ነባርና አዳዲስ የተለያዩ ንግድ ነክ የአስገዳጅ ደረጃዎችና የቴክኒክ ደንቦች መረጃዎችን ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ለማሰባሰብና ለማደራጀት ታቅዶ ከ21(105%) አስፈጻሚ መ/ቤት የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ለ50

ተገልጋዮች በአስገዳጅ ደረጃዎችና ቴክኒክ ደንብ ላይ ማብራሪያ፣መረጃና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በ286 አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች ወይም አግልግሎቶችን እና የሚቆጣጠሩ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችን ለመለየት ታቅዶ 253 (88.4%) መፈጸም ተችሏል፡፡

### 3. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች አፈፃፀም

ከገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ከጥራት ሰርተፊኬት ማሻሻልና ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ላይ ለቀረቡ 26 ቅሬታዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መዘግየትና በፍተሻ ውጤት ሪፖርት ላይ በደንበኞች የቀረበ ቅሬታን ለመፍታት ከኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት እየተሰራ ይገኛል፡፡ አዲስ በተሻሻለው የቆርቆሮ ደረጃ አተገባበር ላይ ከደንበኞች የቀረበ ቅሬታን ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ለመፍታት ተችሏል፡፡

### 4. የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎች

ኮቪድ-19ን ከመከላከል አንጻር ሰራተኞች ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ በኢሜል እንዲመለከቱ በማድረግ አካላዊ ንክኪ እንዲቀንስ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ስብሰባዎች በኦንላይን ማካሄድ የሚያስችል ፕላት ፍርም በመግዛት ሚኒስቴር መ/ቤታችን፣ ክልሎችና ተጠሪ ተቋማት እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡ የሴቶችን የአመራርና የውሳኔ ሰጪነትን ሚና ለማጎልበት በGIZ ድጋፍ በተዘጋጀ የአቅም ማጎልበቻ የ3 ወር ስልጠና ከተቋሙ ለተውጣጡ ከፍተኛ ኤክስፐርት፣ በቡድን መሪዎችና በዳይሬክተር ደረጃ ለሚገኙ 11 ሴቶች ሥልጠናቸውን አጠናቀው ተመርቀዋል፡ ፡ በተጨማሪም ሴቶችን ወደ አመራር ሰጪነት ለማምጣት በተያዘው አቅጣጫ መሰረት በዳይሬክተርነት ደረጃ ከ11 ወደ 12 እንዲሁም በቡድን መሪ ደረጃ ከ25 ወደ 26 ከፍ ብሏል፡፡ የህጻናት ማቆያ ቦታ ተዘጋጅቶ ለህጻናት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን ማህበራዊ ሀላፊነት ለመወጣት በጦርነት ለተጎዱ የአማራና አፋር ክልሎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞችን፣ ተጠሪ ተቋማትንና የንግድና ዘርፍ ማህበራትን በማስተባበር በገንዘብ ከ15.4ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሁም በዓይነት ከ4.08 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት (6000 የቤት ክዳን ቆርቆሮና የምግብና ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች) ድጋፍ በማሰባሰብ ለተፋናቃዮች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ይህ ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን አጠቃላይ ሠራተኛው የአንድ ወር ደመወዙን ብር10.39 ሚሊዮን ለመከላከያ ሠራዊታችን አበርክቷል፡፡

በ2013 የክረምት ወራት በኢንዱስትሪ ፓርኮች የችግኝ ተከላ፣የአቅመ ደካሞች ቤት ጥገና፣ ለመከላከያ ሰራዊታችን የደም ልገሳ እና የመቄዶንያ አረጋዊያን ማዕከልን በመጎብኘት የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡

## 5. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

### 5.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- ✓ የቁም እንስሳት በዋጋ ዝቅተኛ መሆን እና የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት፣
- ✓ የውጭ ሚዲያዎች በሚያስተላልፉት የተዛባ መረጃዎች ገዢዎች የገቡት ውል የማቋቋረጥ ድርጊቶች መበራከት፣
- ✓ ህገወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ በመስፋፋቱ ምክንያት ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶችን በገበያ ላይ መገኘት፣
- ✓ በየቦታው የተቋቋሙ ኬላዎች ለሸቀጦች ነጻ ዝውውር መሰናክል መሆናቸውና ለምርቶች ዋጋ መናር አስተዋጽኦ ማበርከቱ፣

### 5.2 የተወሰዱ እርምጃዎች

- ✓ የቁም እንስሳት የውጪ ንግድ ዋጋ ለማሻሻል የህግ ማዕቀፍ እና የግብይት ስርዓቱ የሚሻሻል የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ በውጭ ሜዲያዎች እየቀረበ ያለውን የተዛባ መረጃ ለመመከት ትክክለኛውን የኢትዮጵያ ወቅታዊ ገጽታ በማስተዋወቅ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት በመንግስት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ በየደረጃው የተዋቀረውን የገበያ ማረጋጋት ግብረ-ኃይል በማጠናከር በህገወጥ ነጋዴዎች ላይ እርምጅ በመውሰድ የማስተካከል ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ አላስፈላጊ ኬላዎች እንዲነሱ ከክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ጋር በትብብር ለመስራት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 6. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤

- ✓ በመንግስት የሚቀርቡ መሰረታዊ ሸቀጦች ሳይቆራረጡ እንዲገቡ ማድረግ፣
- ✓ የኤክስፖርት ምርትን በዓይነት፣በመጠንና በጥራት ለማሻሻል የክልሎችን እና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ማሳደግ፣

- ✓ የሸቀጦችን ነጻ እንቅስቃሴ የሚገቱና ለዋጋ ንረቱ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ያሉ በየቦታው የተቋቋሙ አላስፈላጊ ኬላዎችን ለማስቀረት ከክልሎች ጋር መግባባት ላይ መድረስ፤
- ✓ በኮንትራት እርሻ ያለሙ አልሚ ባህብቶችን ከባለድርሻ አካለት ጋር በመቀናጀት መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ ፤
- ✓ በወጪ ንገድ ኮንትራት ምዝገባ የመግዣ ዋጋ ተመን ላይ ያለውን ችግር ትኩረት ሰጥቶ መፍታት፤

## 7. ማጠቃለያ

የአረጃጀትና ተቋማዊ የለውጥ ስራዎች በተመለከተ የፌዴራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ተከትሎ ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን እና የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን መ/በቶችን ሥራ ከዳኝነት ችሎች ውጭ ያሉትን ሥራዎች እንዲሰራ መተሰጠው ሥልጣን መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱን ከኢንዱስስትሪ ሚኒስቴር በመነጠል እንደገና በማደራጀት Higher Level Map፣ የሚያስፈልው የሰው ሀይል እና የስራ መዘርዝር ተጠናቆ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በመላክ የምዘናና ደረጃ መስጠት ሥራ ከኮሚሽኑ ጸድቆ በመመሪያው መሰረት የድልድል ኮሚቴ ተቋቁሞ የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የሕግ ማዕቀፎችን እና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ጋር በተያያዘ የችርቻሮ የመሸጫ ዋጋው በኢኮኖሚውና በህብረተሰቡ ላይ የጎላ ተጽእኖ እንዳይፈጥር በመንግስት እየተወሰነና ቁጥጥር እየተደረገበት ሲሰራ የቆየ ቢሆንም የሀገር ውስጥ ነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ የዓለም አቀፉን ዋጋ በሚያንጸባርቅ መልኩ እየታየና በየጊዜው እየተከለሰ ወደ ሸማቹ እንዲተላለፍ ባለመደረጉ በዋጋ ማረጋጊያ ፈንዱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ዕዳ እየተከማቸ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ከነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ጋር በመሆን ከላይ የተስተዋሉትን ችግሮች በሚፈታ መልኩ የነዳጅ ውጤቶች መሸጫ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀትና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቦ ምክር ቤቱ ታህሳስ 20 ቀን 2014 ዓም ባደረገው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ጸድቆ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ በተቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ አማካኝነት ክልሎችን ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈጸም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የነዳጅ ውጤቶች የዋጋ ግንባታና ትርፍ ህዳግ አሠራር በተያያዘ በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያለው የነዳጅ ዋጋ ማሻሻያ ላለፉት 25 ዓመታት በስራ ላይ የቆየ መሆኑን ተከትሎ ነባሩ አሰራር ያለበትን ክፍተት መፈተሽና ማስተካከል አስፈላጊ በማስፈለጉና ወጥነትና ግልጽነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኂላ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቦ ምክር ቤቱ ታህሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ባደረገው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ጸድቆ በውሳኔው መሠረት ወደ ሥራ ለመግባት ኩባንያዎች ማዘጋጀት የሚገባቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንዲሰሩ የኢትዮጵያ የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ጉዳዩን በዋናነት በመያዝ በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

የቁም እንስሳትን ከዋጋ በታች አሳንሶ በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ግኝታችን ማሳጣትና የኮንትሮባንድ ንግድን ለመግታት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ የቁም እንስሳት ላኪዎች የእንስሳት የግብይት ዋጋ ወቅታዊና ተዓማኒ መረጃዎች እንዲኖራቸው ለማድረግ ከላኪዎችና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተውጣጣ ኮሚቴ ከሚመለከታቸው በማቋቋም የቁም እንስሳት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ጥናት እስከሚካሄድ ድረስ ለ3 ወር የሚቆይ ቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ መመሪያ ቁጥር 863/2014 ተዘጋጅቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጸድቆ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ የቁም እንስሳት ላኪዎች የእንስሳት የግብይት ዋጋ ወቅታዊና ተዓማኒ መረጃዎች እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ ከላኪዎችና ከሚኒስቴር መ/ቱ የተውጣጣ ኮሚቴ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ከተደረገ በኂላ የቁም እንስሳት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ጥናት እስከሚካሄድ ድረስ ለ3 ወር የሚቆይ መመሪያው ተዘጋጅቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጸድቋል፡፡

ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶችንና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምርቶች ባቀረቡ ድርጅቶች ላይ 10 ኩንታል በላይ የተለያየ ዓይነት የምግብ ጨው፣የወተት ጣዕም ያለው የማንጎ ጭማቂ፣ የእጅ መታጠቢያ ፈሳሽ ሳሙናና ኤሪያል የዱቀት ሳሙና እና ከ13 ኩንታል በላይ ጥራቱን ያልጠበቀ ስኳር ምርት የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየን ላይ በተደረገው የጥራት የቁጥጥር እና ከህብረተሰቡ በደረሰ ጥቆማ መሰረት ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት ምርቶቹ ወደ ገበያ እንዳይገቡና እንዲወገዱ በማድረግ በህብረተሰቡን ጤንነት ላይ ሊደርስ የሚችል የቴና ችግር ለመከላከል ተችሏል፡፡

የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን በሚያባብሱ ህገወጦች ላይ በየደረጃው በተዋቀረው ግብረ ሀይል እርምጃዎችን በመውሰድ ገበያውን ለማረጋጋት በተሰራው ሥራ በአጠቃላይ ብር 7,773,280 በገንዘብ ከተቀጡ ነጋዴዎች ላይ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

ዘርፉን በቴክኖሎጂ ለማዘመን በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት 1,134 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ጣቢያዎች መካከል 1,082 ጣቢያዎች ከአንድ መረጃ ቋት እንዲያገኙ በማድረግ ከክልሎች ለመናበብ አስችሏል፡፡

የወጪ ምርቶች አፈጻጸም ሲታይ ባለፉት 7 ወራት 2.353 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.166 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር (92%) ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ከተገኘው 1.812 ቢሊዮን ዶላር ጋር ሲነጻጸር በ353.5 ሚሊዮን ዶላር (19.5%) ጭማሪ አሳይቷል፡፡

የቡና ማምረት፣ መሰብሰብና ማዘጋጀት ላይ በተሰራው የድጋፍና ክትትል ስራ የቡና ጥራት እንዲሻሻል እና የምርት አቅርቦቱ እንዲጨምር በመደረጉ፣ በዝቅተኛ ዋጋ ሲሸጥ የነበረው ቡና ዝቅተኛ የዋጋ ተመን ተግባራዊ በመደረጉ እና ከአበባ ምርት ጋር በተያያዘ የአውሮፓ ገበያ መዳረሻን ትኩረት አድርገው የሚሰሩ አምራቾች በተለይ ኢኳዶርና እና ኬንያ ካለፈው የፈረንጆች ዘመን መለወጫ ጋር ተያይዞ አቅርቦቱን በማሳነሳቸው ለሀገራችን አምራቾች የተሻለ ዋጋ እንዲያገኙ ማስቻሉ እና በሶማሌ ላንድ ያለው የፍራፍሬ ፍላጎት ከፍተኛ ሆኖ መገኘቱ በተለይ ወደ ጎረቤት ሶማሊያ ይላካል ተብሎ ከሚጠበቀው በላይ በመጨመሩ ለገቢው ጭማሪ ምክንያት ሆኗል፡

የሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓትን ከማጠናከርና ከማዘመን አንጻር ከ1.12 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና በገበያ ላይ የሚገኙ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ልዩ ልዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ታቅዶ 798,753 (70.9%) የተከናወነ ሲሆን 2,005 የፈሳሽ ማጓጓዣ ቦቴዎችን ታንከር ይዘት ለማረጋገጥ ታቅዶ 1,611 (80.4%) የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡

አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው የገቢ ምርቶች ላይ የጥራት ቁጥጥር በማካሄድ የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት ማስተበቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡

በዚህም መሰረት 1,600,000 ሜትሪክ ቶን የገቢ ምርቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ11,633,026.69 (102%) ሜትሪክ ቶን የገቢ እቃዎች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ይህ አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወራት ጋር ሲነጻጸር የ8.43% ጭማሪ አሳይቷል፡፡